# ታሪክ ያላት ሃገር ያለመሪ ስትቀር

## ታደለ መኩሪያ

## April 29, 2008

ሰዘመናት በሕግ ሲተዳደር የኖረን ሕዝብ በየጊዜው ሃገር ወለድ አምባገነኖች እየተነሱ ሲጮቅኑት ብሩሕ ረዕይ ያላቸውን ዜጎች ሲያጠፉ ታይቷል።
ይህቺን ታሪክ ያላት ሃገር መሪ አልባ ሕግና ሥረዓት የጎደላት መስላ እንድትታይ አድርገዋታል። በቅርቡ በፓላማና ቀበሌ ማሚያ ስም በሃገር አቀፍ የተካሄደው ምርጫ ጥሩ ምስክር ነው። ‘እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው’ መሰል ምርጫ በማስፈራራት በድብደባና ወከባ ተጠናቋል። ቀደም ሲል ለውድድሩ ቀርበው የነበሩት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድብደባውንና አፈናውን በመፍራት አቋርጠው ሲወጡ መራጩም ሕዝብ የዜግነት መብቱን እንዳይወጣ ተስፋ ቆርጦ ከቤት እንዲውል ተደርጓል። ይህን መሰሉ ድርጊት እስከመቼ ይቀጥላል? የሕዝቡስ ዝምታ መቼስ ያበቃል?

በሃገር ውስጥ በሰላማዊ ትግል ለውጥ ለማምጣት የሚቀሳቀሱት የፓለቲካ ድርጅቶች የሰላም ዘንባባ ይዘው በጋራ ተባብረን ሃገራችንን ከኋላ ቀርነት ከረሃብና ሰቆቃ እናውጣት የዘር ክፍፍሉን እናቁም ብለው የወያኔን መንግሥት ቢማጸኑም ፤ ጥያቄቸው ከወንጀል ተቆጥሮ ወደእስር ቤት ተወርውረዋል።ድምፃችን ይከበር ብለው ሰልፍ የወጡትም በመከላከያው ሠራዊት ከተገደሉና ከቆሰሉ በኋላ የታሠሩት የሕዝብ መሪዎች ከነአካቴው በወያኔ ብሶ ለድፍረታቸው ይቅርታ እንዲጠይቁ ተደርገዋል። እንቢተኝነቱና ትዕቢቱ ምዕላተ ሕዝቡን መናቁ ዋና ምንጩ የመከላከያ ሠራዊቱ ተጠሪነቱ ለወያኔው ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ እንጂ ለሕዝብ ያለመሆኑ ነው።

በሰኔና ሕዳር 1997 ዓመተ ምህረት ምርጫው አስመልክቶ ለተነሳው አንባጓሮ የመከላከያው ሠራዊት ታንክ መትረየስና ክላሽኮቭ ጠመንጃ ተጠቅሞ ጦር ሜዳ መሰል ጭፍጨፋ በወገኑ ላይ መፈጸሙ ያንን የሚያረጋግጥ ነው።

ብዙዎቹ የአፍሪካ አገራት ነፃ ሣይወጡ የቀድሞው የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት በተባበሩት መንግሥታት ሥር ኮሪያና ኮንጎ ዘምቶ በውትድርና ሞያውና ሥነምግባሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅናን ያገኘ ሠራዊት ዛሬ የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲሰ አበባ የዓለም ሕዝብ እያየው በታንክና በመትረየስ ሕፃናት፣ ሴቶች፣ ተማሪዎች ፣ሐረጋውያንን፣ ወዘተ ተኩሶ ሲገድል ማየት የሚያሣዝን፣ የሚያሣፍር፣ የሚያስፈራ፣ የሕዝብ መከላከያ ሠራዊት ያለመሆኑን የሚያሳይ ነው።
የእኛን ዓይነት የምርጫ ውዝግብ በኬኒያ በተከሰተ ወቅት የመከላከያው ሠራዊቱ እጁን አላስገባም። ይህም የሚያሳየው የሰለጠነና ደረጃውን የጠበ የሕዝብ ሠራዊት መሆኑን ነው።

ይህ የወያኔ የመከላከያ ሠራዊት በሥልጠናው ወቅት ያልተገለጸለት ሐቅ አለ። ይሄውም ከታጠቀው የወገቡ ቀበቶ እስከ ቦንብ ጣዩ አይሮፕላን እናት አባቱ ያለጫማ ባዶ እግራቸውን እየሄዱ ከእህቱና ወንድሙ አፍ እየቀሙ በከፈሉት ግብር መገዛቱን ነው።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ታርዞ፣ተርቦና ተጠምቶ በውጪ ምንዛሬ የመከላከያ ሠራዊቱን ማስታጠቁ ራሱን መልሶ እንዲያጠቃው አይደለም። ልጆቹንም ወደ መከላከያው ኃይል እንዲቀላቀሉ፡መፍቀዱ፡ሃገርን እንዲያገለግሉ፣ ወሰንን እንዲያስከብሩ፣በኢትዮጵያዊነቱ እንዲያኮሩት እንጂ ለሥልጣን ጥመኞች ዘብ እንዲቆም አይደለም።
በአሁኑ ወቅት በሰላም የሚቀሳቀሱት የፖለቲካ ድርጅቶች የሃገራችንን ችግር በሰላምና በዲሞክራሲ መንገድ እንፍታ ሲሉ፤ እርስ በእርሳችን በሐንዱራ ሐብታችን ከውጭ አገር በገዛነው መሣሪያ አንጨራረስ ማለት ነው።ለሥልጣን ሽኩቻ ለሚደረገው ይሰጥ አገባ ፡ አንድ ወታደር እንኳን አይሙት፤ እርሱም ለሃገር መከላከያ በታጠቀው መሣሪያ በሕዝብ ላይ አያዙር ማለት ነው።

ለአንዳፍታ ቆም ብለን ከግንቦት 1997 ዓ ም ወዲህ ሕዝቡ በሰላማዊ መንገድ መንግሥት መለወጥ ይቻላል ብሎ ጦርነትን ካወገዘ በኋላ ወያኔ ለሕዝብ ድምፅ አልገዛም በማለቱ ስንት ወገን በሠራዊቱ ተገደለ? ስንት ሠራዊትስ ሞተ? ምን ያህል ንብረትስ ወደመ?
ለምሳሌ በኦጋዴን ፣በሰሜን፣በደቡብ ፣በምዕራብ፣ በምስራቅ በአራቱም ማዓዘናት የሚካሄደው ልማት አይደለም ጦርነት ነው።የምንሰማው የምናየው ጥጋብ አይደለም ረሃብ ነው። የሱማሊያን ወሰን ተሻግሮ የዘመተው የመከላከያ ሠራዊትስ? በለስ ቀናው? በመቅድሾ ጎዳናዎች እሬሳው እንደውሻ ሬሳ ሲጎተት ነው የምናየው። ግንቦት 1997 ዓ ም የተካሄደው ምርጫ ውጤቱ ተከብሮ ኖሮ ይህ በደል ይደርስበት ነበር?
እ ኤ አ 1994 ዓ ም የአሜሪካ ሠራዊት አባል የሆነ አንድ ግለሰብ እንደዛሪዎቹ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባሎች በመቅድሾ ጎዳና በመጎተቱ ምንም ሳታመነታ ኃያሏ አሜሪካ ጓዟን ጠቅልላ ለመውጣት ተገዳለች። ይህም የሚያሳየው ለዜጎቻቸው የቱን ያህል ክብር እንዳላቸው ነው። ወያኔ ግን ለሠራዊቱ ግድ የሌለው ገና ሺዎች ሬሳቸው እሰከ ሚጎተቱ ነው የሚጠብቀው። የመከላከያው ሠራዊትስ ነግ በኔ ያለማለቱ ለምድነው? ሕዝቡስ ልጆቹን በሰው አገር ልኮ የሚስጨርስበትን የወያኔን መንግሥት ያለመጠየቁ? ይህ ሁሉ ግፍ የሚፈጸመው የቆራጥ መሪ መጥፋት የእያንዳንዱ ግለሰብ ለመብቱ ያለመቆም ሌሎች በከፈሉት መስዋዕትነት ነፃ እወጣለሁ ብሎ በመታሰቡ ነው።

ታደለ መኩሪያ
April 29, 2008